# ✝ የመናፍስት መደበቅ ✝

## ክፍል 1•

በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ፣ አሜን። አቤቱ የሠራዊት ጌታ ቅዱስ የሆነክ አምላካችን ሆይ፣ እስከዚህቸ ግዜና ሰዓት ስላደረስከን እናመሰግናለን። ቀሪው ግዜያቶቻችንም ሁሉ ባርክልን። መለኮታዊ ፍቅርህንና ሰላምህን ለሕይወታችን በየግዜው ታክፍለን ዘንድ እንማጸናለን። በቸርነትህ ኃይልና በጥበቃህ ጥላ ውስጥ ዘመኛችንን ጎብኘው። ነፍሳችንን ቀድሳት። ሥጋችንንም ለነፍሳችን ማደሪያነት የበቃ የተባረከ ታደርገው ዘንድ ከበረከትህና ከብርሃን ረድኤት ታካፍለን ዘንድ እንለምናለን። የተሰወሩ ጠላቶቻችንን ተቋቁመን በመ'ቀደስ አኗኗር እየታደስን ሁልግዜ ከአንተ ጋር እንኖር ዘንድ በቅዱስ ልጅህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም። በቅድስት እናትህ እመቤታችን ድንግል ማርያም ስም። አሜን።

✞✞✞

ዲያቢሎስ በመጀመሪያው ወደ ሰው ልጅ የመጣበት ግዜን ስንመለከት በእባብ አካል ውስጥ ተደብቆ እንደሆነ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት ያስረዳናል። መደበቅ እንግዲህ የጠላት ጠባዩ ነው። አድብቶና አሸምቆ እንጂ እንዲሁ በቀጥታ እንዳገኘ ፊት ለፊት የሚያጠቃ አይደለም ዲያቢሎስ። የሚከለልበትና ምሽግ የሚይደዝበት አንዳች መደበቂያን ሁልግዜ ይፈልጋል።

✞✞✞

በእባብ አካለ ሥጋ ተደብቆ የመጣው ዲያቢሎስ፤ አዳምና ሔዋን ከሕይወት ዛፍ እንዲበሉ ካሳታቸው በኋላ ክፉና ደጉን በለዩ ግዜ ዓይኖቻቸው ተከፈቱ። ራቁቶቻቸውንም እንደሆኑ ተገነዘቡ። ስለዚህም በዛፎቹ መካከል ከእግዚአብሔር አምላክ ተደበቁ።

✞✞✞

ዛሬም በቤትና በኑሮአቸው ውስጥ የተደበቁ ሰዎች በጣም ብዙ ይሆናሉ። አሁን መደበቅ ስንል በአንደኛው ከዓለምና ከሰው መሸሽ አንደኛው ነው። በሁለተኛው የውስጣዊ ሕይወታቸው ጸጋና ኃይል የተደበቀባቸውም አሉ። በማኅብረሰብ መካከል እየኖሩ ግን ከማኅበረሰቡ ተደብቀው የሚኖሩ ሰዎች በዘመናችን ጥቂት አይደሉም። ሰው የሚሸሹ፣ ፍቅር የሚሸሹ፣ ደስታ የሚሸሹ፣ ትዳር የሚሸሹ፣ ብርሃን የሚሸሹ፣ እውነት የሚሸሹ ሰዎች ውስጣዊ ሕይወታቸው ከእግዚአብሔር አምላክ የኃይልና የግንኙነት መስመር የተደበቀባቸው ሆነው ማንም ችግራቸውን በውል ሳይረዳላቸው በራሳቸው ዓለምና ምናብ የተደበቁ ዜጎች አሉ። ዲያቢሎስ አንዴ ወደ ሕይወትህ ተደብቆ ከመጣ በኋላ ያንኑ የመደበቅ ገጽታና ምልክት ለኑሮህም ያወርስሃል። ሰማያዊ ሚስጢር ይደበቅብሃል። የሃይማኖት ፋይዳና የእምነት እውነቶች ይደበቁብሃል። ፍቅርና ሰላም ከውስጥህም ይደበቁብሃል። ደስታና ጸጋ ከባህሪያቶችህ ውስጥ ይደበቃሉ። ዛሬ ላይ አብዛኞቻችን በረከትና ሞገስ ከአኗኗራችን ፍሬ ተደብቋል። ያልተገለጠና የተሰወረ ጠላት በተገለጠና በሚታይ ጥቃት ሕይወታችን በተለያዩ የመከራ መንገዶች ላይ ረጅም ርቀት እንዲጓዝ ያስገድደዋል፡

✞✞✞

መንፈስ ያንተ የነፍስ አቅጣጫ በሥጋ ጓዳና ውስጥ እንዲደበቅ አሸምቆ በግዜ መካከል በተጠና ሥልት ከመሥራቱ አስቀድሞ በአንተ ውስጥ የሚደበቅበትን ሥፍራ ይፈልጋል። እንደ ምሽግ የሚጠቀምበት ያንተ የሆነ ነገር ይፈልጋል።

✞✞✞

ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6፥12 ላይ ያለውን ቃል ስንመለከት እንደዚህ የሚል ነገር ተጽፎ እናገኛለን። << መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካሉ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። >>
#መጋደላችን የሚለው ቃል የሚያስረዳን በእኛና ደምና ሥጋ ካለበሱ፣ አለቃና ባለሥልጣን የሆኑ፣ የጨለማው ገዢዎች የሆኑ፣ ሰማያዊያን ከነበሩት ከክፉ መናፍስት ጋር ያለውን ጦርነት ነው። ጦርነቱ እስከመጋደል የሚያደርስ እንደሆነ መጋደላችን በሚለው ቃል ውስጥ ተገልጾ የሚገኝ የማስጠንቀቂያ ደውል ነው። ይሄ የሞት ሽረት ጦርነት ሲካሄድ መንፈስ << የውጊያ ሜዳ >> የሚያደርገው ያንተን ሕይወት ነው። የፍልሚያው ስፍራና ሁኔታ ባንተ ኑሮ ላይ ነው የሚካሄደው። የምትዋጋው መንፈስ ነውና በግዙፈ አካል በሚገኝ ስፍራ ውስጥ አይደለም ቦታ ይዞ የሚታገልህ። የምሽጉ መደበቂያ አንተ ነህ። አሸምቆ የሚያጠቃበት መከለያ ያንተ ሕይወት ውስጥ ካለው ነገር በመነሣት ነው።

✞✞✞

ስለዚህ አንደኛው ልንነቃ የሚገባው መሠረታዊ ጉዳይ ምንድነው ማለት ነው?
መናፍስት በኛ ዘመን፣ ግዜና ኑሮ ውስጥ ተደብቀው እንደሚዋጉን ልንነቃ ያስፈልገናል ማለት ነው።
በመጀመሪያው ስናስታውስ ወደ ሔዋን ዲያቢሎስ ሲመጣ በእባብ አካል ውስጥ ተደብቆ ነው። አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር በመኖር ውስጥ ባለጸጋ ስለነበሩና መለኮታዊ ጥበቃውን ይዘውት ስለነበረ ውስጣቸው መደበቅ አልቻለም። ስለዚህም ከውጪ ባለ አካል ተደብቆ መጣ። ከሕይወት ዛፍም ከበሉ በኋላ ልባቸው ክፋትንና ደጉን ለመለየት ይቻል ዘንድ ሆነ። ከዚያች ግዜም አንስቶ ክፋትን ባወቀ ልባችን በኩል ዲያቢሎስ ውስጣችን የሚደበቅበትን እድል አገኘ። "ምድርን ዳግመኛ ስለ ሰው አልረግምም፥ የሰው ልብ አሳብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉ ነውና፤"
(ኦሪት ዘፍጥረት 8፥21)
በሰው ልብና ሕይወት ውስጥ በመደበቅም የመጀመሪያውን የከሳሽነት ጠባይ በአዳም ልጅ በቃየን እንደገለጠ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የምንገነዘበው እውነታ ይሆናል።

✞✞✞

ዲያቢሎስ በሕይወትህ ውስጥ በግዜህ መካከል ከመደበቁ በፊት ወደ ዘመንህ ሊመጣ ያስፈልጋል። በቃ ከዛ በኋላ ባላጋራ መሆን ይጀምራል። በ1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 5፥8 ላይ "ባላጋራችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ በዙሪያችሁ ይዞራል" የሚለው ቃል ዲያቢሎስ ባለጋራ እንደሚሆን ማሳያ ነው። ባለ-ጋራ ነው የሚለው። የሚጋራ ማለት ነው። ዘመንን፣ ግዜን፣ ኑሮን፣ አሳብን፣ ሕሊናን፣ ልቦናን፣ ሰውነትን፣ ዕድልን፣ ጸጋን፣ እውቀትን፣ ገንዘብን፣ በረከትን፣ ሞገስን፣ ቤትን፣ ቤተሰብን ሁሉ የሚጋራ ነው። ተጋርቶህ ሲኖር ሊያሻሽልህ ወይ በደረጃ ከፍ ሊያደርግህ አይደለም የሚቀመጠው። የተጋራህን ነገር ሁሉ ሊያጠፋውና በመጨረሻውም አንተን ሊያጠፋ ነው የሚታገለው።

✟✟✟

በዚህ የጥፋት ግዜውና ሥልቱ ወቅት ትልቁ መሣሪያው በሕይወትህ ውስጥ ተደብቆ የመቆየት አቅሙ ነው። ታዲያ መንፈስ ምን ምን ውስጥ ይደበቃል የሚለውን ስንመለከት የሚከተሉት ውስጥ የማድፈጥና ተከልሎ የመቆየት ጠባያት አሉት።
❶• እውቀት ውስጥ
❷• ልማድና ባህሪይ ውስጥ
❸• የቤተሰብ ልማድና ባህሪይ ውስጥ
❹• ኃጢአት ውስጥ
❺• የአከባቢና የገጠመኞች ችግር ውስጥ መናፍስት ይደበቃሉ።

በሚቀጥሉት አምስት ክፍሎች እያንዳንዱን የመናፍስት ድበቃዎችን በዝርዝር እንመለከታለን።

በርቱ።
#ጸባኦት_ይከተላችሁ

## ✝ የመናፍስት መደበቅ ✝

## ክፍል 2•

በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ፣ አሜን። የሰማይና የምድር አባት ልዑል እግዚአብሔር ሆይ፣ በዚህ ግዜና በመለኮትህ ፍቅርና ጥበቃ ውስጥ ስላቆምከን እናመሰግናሃለን። ሰማያዊ ቸርነትህና ብርሃንህ አይለየን። አቤቱ አምላካችን ልዑል ጌታ ሆይ፣ መውጣት መግባታችንን ትጠብቅ ዘንድ እንለምናለን። በምስጋናው ቦታ ሁሉ እንገኝ ዘንድ ብርታትን አድለን። ሰማያዊ ቃልህንና እውነትህን ለኑሮአችን ታካፍለን ዘንድ እንማጸንሃለን። አገራችንንና ሕዝቧችን ጠብቅልን። በቅዱስ ልጅህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም። በቅድስት እናትህ እመቤታችን ድንግል ማርያም ስም። አሜን።

✟✟✟

## ✝ እውቀት ውስጥ የሚደበቁ መናፍስት ✝

መንፈስ በተፈጥሮ ባህሪውና ገጽታው የሚጨበጥ አሊያ የሚዳሰስ ጠባይ የለውም። ረቂቅ አካል ነውና በሥጋ ዓይን የምናየው፣ በሥጋ ጆሮ የምንሰማውና በሥጋ እጅ የምንነካው አይደለም።
ይህ የመንፈስነት ባህሪይ ለርኩሳን ኃይሎች በሰው ልጆች ሕይወትና ዘመን ውስጥ የመደበቅና የማሸመቅ ዕድልን ለማስፋት አስችሏቸዋል። በተለይ መስገድ መጸለይ ለማያውቅ ሰው አኗኗሩ ደግሞ ለአጥቂ መናፍስት በጣም የተመቸና ስለመመሸጋቸው ምንም መረጃ ላለመስጠት የሚያስችላቸውን የመደበቅ ባህሪያቸውን የሚያግዝላቸው የአኗኗር አካሄድ ነው።

✟✟✟

የትኛውም የመንፈስ ስምሪት በየትኛውም መንገድ ወደ ውስጣችን ከገባ በኋላ በውስጠኛው ሕይወታችን ውስጥ የሚደበቅበትን አንድ የኛ ነገር በጣም ይፈልጋል። ምሽግ ይዞ የሚጫወትበት ቦታ ከሌለው የዘመናችንን ሥር መያዝ ስለሚከብደው የግድ አንድ እኛኑ መስሎ የሚሸሸግበት የኛ የሆነ ነገር ማግኘት ይፈልጋል። የሚደበቅበትን ቦታና ግዜ ካገኘ በኋላ በቃ፤ የተደበቀበትን ቦታ አይነካውም። ነቅተህ ምሽጉን እንድታፈርስበት ስለማይፈልግ የሚከለልበትን ቦታ አይረብሸውም። በአንፃሩ ሊያበለጽገውና ሊያደላድለው የሚፈልገው ክፍልህ ነው የሚሆነው።

✞✞✞

መንፈስ በውስጣዊ ማንነታችን ውስጥ የት ይደበቃል የሚለውን መሠረታዊ ጉዳይ ስናነሣ በመጀመሪያ የምንመለከተው እውቀታችን ውስጥ የሚደበቁ መናፍስትን ይሆናል።

✞✞✞

እውቀታችን ውስጥ የተደበቁ መናፍስት ስንል ምን ማለታችን ነው? እውቀት ውስጥ የተደበቁ መናፍስት ማለት በአእምሮአችን ውስጥና በልቦናችን መዝገብ ውስጥ ባውቅነው ልክ መጠን የተከለሉ ጠላቶቸ ማለታችን ነው። አስቀድሞ እንደተመለከትነው መንፈስ ሊደበቅበት የሚፈልገው ቦታ የኛ የሆነው ነገር ላይ ነው። ስለዚህ እውቀታችን ውስጥ በሚደበቅበት ግዜ ያለንን እና የምናገኘውን እውቀት ተንተርሶ የሚመሽግ ጠላት ነው ማለት ነው።

✞✞✞

በግልጽ ምሳሌ አንድ ሰው በጣም ስለ እጽዋት ምርምር ያውቃል እንበል። መንፈሱ ከውስጡ በሚኖርበት ግዜ እንደ መመሳሰያ የሚጠቀምበት አንዱ መንገዱ ያለው የምርምር ደረጃ ላይ በመንጠልጠል ነው። ባለሙያው በዚያ የምርምር ዘርፍና ጥናት ላይ ለረጅም ዘመን ግዜውን እንዲያጠፋ ሌሎች የሕይወት እይታዎቹን በማደብዘዝ አንድ የምርምሩ ጉዳይ ላይ ብቻ እንዲመሰጥ በማድረግ ምንም በማያስተውልበት መንገድ ከሰማያዊ ዜግነት በጥበብ እያራቀው ይመጣል። ከእግዚአብሔር ኃይልና መንፈሳዊ ግንኙነት ለማሸሽ ሲንቀሳቀስ ታዲያ በጣም በዝግታና ቀስ በቀስ ያሉትን ትናንሽ መንፈሳዊ ክሮችን በመበጠስ ይሆናል። በምሳሌ ተመራማሪው ግለሰብ አስቀድሞ መስገድ መንበርከክ የሚያውቅ ከነበረ፤ በምርምሩ በኩል ጫና እንዲፈጠርበት በማድረግ ግዜ እያሳጣ እያሳጣ በዝግታ ከአምልኮት ሕይወት እንዲለይ ያደርገዋል። አንዳንድ ግዜ ብልጠቱ ምን ያደረጋል፤ የጸሎት ሰዓታችንና የአምልኮት ግዜያችን እንዲቀንስ ዙሪያችንን መልካም ያደርገዋል። የምናካሂደው የጥናት ምርምርና መሰል ጉዞ አልጋ በአልጋ #ለግዜው እስከሆነ የግዜ ቆይታ ያደርገዋል። ስለዚህ ትንሽ ጸልየን ብዙ የምናተርፍ እንዲመስለን ሥራችንን ውጤታማ እንደሆነ አድርጎ ያሳየናል። በዚህ ግዜ በጥንቃቄ የሚፈጥረው ምንድነው የሥራና የውጥረት ጫና ነው። እየተሳካልን በሚመስለው ግዜ ውስጥ ስኬቱ እንዳያመልጠን እንድንሯሯጥና ለአምልኮተ እግዚአብሔር እንድንዘገይ ቁናትን እያጠበቀ ይሠራል።

✞✞✞

በጣሚ በሚገርም ሁኔታና አኳኋን ደግሞ አንዳንዴ መናፍስት ስለ ራሳቸው መንፈሳዊ እውቀት ባለን መረጃና አረዳድ ውስጥ የሚደበቁበት ግዜ አለ። ለምሳሌ ሰውየው በደንብ ስለ አምልኮት ሕይወት የሚያውቅ፣ ስለ ስግደትና ጸሎት የተረዳ፣ በቤተክርስቲያን መሠረታዊ እወቀቶችና መረጃዎች የዳበረ ሰው ሊሆን ይችላል።

አሁን መንፈሱ አብሮት በሚኖርበት ግዜ እነዚህን እወቀቶቹን አይነካበትም። ስለራሱ የመንፈሱ ክፉ ባህሪይና ሚስጢራዊ ዘዴ ሰውየው እውቀት እያገኘና እየተማረ ሲሄድም መንፈሱ በሚገርም ሁኔታ አብሮት ይማራል። ያለውን እውቀት የሚቃረነው ነገር ካደረገ እንደሚነቃበት ስለሚያውቅ መናፍስቱ በዚህ ሰውየው ጠንካራ በሆነበት ነገር ላይ ጫና አይፈጥሩም። ይልቁኑ እንዲበረታበትና እንዲገፋበት ምናባዊ እይታዎችን እየሳሉ ወደ ቲዎሪና የንድፈ አሳብ ሚዛኑ በደንብ እስከሚያጋድል ድረስ እየቦረበሩ እየበረቦሩ በቀስታ ይሠራሉ።

✝✝✝

ብዙ ሰዎች ስለ መሠረታዊ የአምልኮት ሕይወትና የመናፍስት ውጊያ የተለያዩ ጥሩ እወቀቶችን ስላጠራቀሙ መናፍስትን የሚቆጣጠሩ የሚመስላቸው ይኖራሉ። ይሄም አንዱ የመናፍስቱ ሥልታዊ መንገድ ነው። አሁን አንዳንድ ግዜ ሰዎች ጸሎት ቤት ሰርተው ውጊያ ይጀምሩና ብዙ መንፈሳዊ አቅምና ኃይል እያገኙ በሚመጡበት ወቀት ይኸው መንፈሳዊ ኃይላቸው ወደ መረጃና እውቀት እያዘነበለ ይመጣል። በዚህ ግዜ በማስተዋልና በማጤን ተረጋግተው ካልተመላለሱ መንፈሱ ያላቸውን የአምልኮት መረጃ ወደመሬት እንዳያወርዱት ብዙ የሚማሩ አሊየም ብዙ የሚያስተምሩ ሰዎች ያደርጋቸዋል። ስለዚህ ከተግባር ይልቅ በእውቀት ላይ ብቻ የተመሠረተ ውጊያን እንዲያደርጉ የኑሮ መስመራቸውን በግዜ ውስጥ እያዘመመው እያዘመመው ይመጣል።

✝✝✝

መናፍስት እውቀት ውስጥ በሚደበቁበት ግዜ በጣም አደገኛው ክፍል ሰውየውን ይኮፍሱታል። ለራሴ እኔ ራሴ አውቃለሁ አይነት ብቻ የሚል ገጽታ ከባህሪያቸው ውስጥ አይጠፋም። በተለይ መንፈሱ እውቀታቸውን እያበለጸገና እያሳደገላቸው ከሄደ፤ ብዙ እወቀቶችንና ልምዶችን ያካበቱ ከሆኑ በፍጹም የራሳቸውን የተግባር ችግር መመልከት አይፈልጉም። መንፈሱ የተደበቀበት እውቀታቸውም ሲነካ በጣም ይቆጣሉ። "መስገድ እኮ ቀንስሃል? ለምን ተውክ?" ብላችሁ ስትጠይቋቸው "አንተ ነግረኸኝ ነው የምሰግደው? ስለ ስግደት አውቃለሁ!" አይነት ዝግት የሚያደርግ መልስ ይሰጣሉ።
እሺ አምልኮት ውስጥ የተገኙ ሰዎች በእውቀቴ ልክ የተደበቀ መንፈስ አለ የለም የሚለውን ለመለየት ምን ማድረግ አለባቸው? ራሳቸውን << በተግባር መመርመሪያ >> ውስጥ አስገብተው ማየት ያስፈልጋቸዋል። እንዴት ነው ሕይወቴ? እየሰገድኩ ነው ወይ? በምችለው ግዜ ሁሉ እየተንበረከኩ ነው ወይ? ስጀምር በነበርኩበት የአምልኮት አቅምና ጉልበት ነው ዛሬ ላይ የተገኘሁት ወይ? የምግባር ክርስትናዬ ተቀዛቅዟል ወይስ በርትቷል? ብለው በመፈተሽ በደረጃ እረከናቸው ልክ ያደፈጠ ጠላት እየሰራ ስለመሆኑና ስላለመሆኑ ማስተዋል ያስፈልጋቸዋል።

✝✝✝

መናፍስቱ የተደበቁት በዓለማዊ እውቀታችንና ከአምልኮተ እግዚአብሔር ውጪ ባለ መንፈሳዊ መረጃችን ውስጥ ከሆነ አደገኛነቱ በጣም ይጨምራል። በብዛት የሲዖሉ መንፈስና የጠቋር መንፈስ ይህንን እውቀት ውስጥ የመደበቅ ጠባያት ይይዛሉ። የሲዖሉ መንፈስ ከሆነ፤ ግለሰቡን ዓለማዊ እወቀቶች ላይ በጣም የዳበረ መረጃ እንዲኖረውና የአስተሳሰብ ደረጃው ከፍ ያለ እንዲሆን ያግዘዋል። አሁን ሰውየውን እንዴት ነው የሚሸውደው፤ ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅም እውቀት እንዲጀምርና እንዲሠራ ቦታ ይለቅለትና አብዛኛውን ግዜውና አቅሙን እዛ ላይ እንዲስብ ያደርገዋል።

ብዙ በመሥራት ብዙ እንደሚገኝ ብቻ አድርጎ የኑሮ ዘይቤያቸውን ስለሚያጠበው በሕይወት ጎዳናዎች ላይ ረጅም ርቀት ሮጠው እንዲጠፉ ሥልትና እቅድ ያመቻቻል። የእግዚአብሔር ቃል የሚለው <<ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ ነው።።>> አለቀ በቃ። አስቀድማችሁ እኮ ነው። በአንደኝነት የኑሮ መሠረታችን መገንባት ያለበት እዚህኛው ፍለጋ ላይ ነው። ዘወትር በየቀኑ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ሰማያዊ ዜግነት መፈለጋችንን መላልሰን መጠየቅ አለብን። ከዚያ ሁለተኛው ይቀጥላል። ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል ነው የሚለው የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ስድስት ወደ መጨረሻው ላይ። የሚጨመረው የሚከተለው ከፍለጋው በኋላ ነው። የሚቀድም አይደለም።

✟✟✟

ዛሬ ብዙ የዓለማችን ሰዎች አስቀድመው የሚፈልጉት የሚጨመረውን ነው። እውቀት፣ ዝና፣ ባለጠግነት፣ ችሎታና መሰል ነገሮችን በመጀመሪያ ሲፈልጉ መቅደም የነበረበትን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ ሳያገኙ ዘመናቸው ያልቃል። ለዚህ መካን የሆነ ኑሮና ዘመን ደግሞ ዋነኛውን ድርሻ የሚጫወቱት መናፍስት በአንደኛው እውቀት ውስጥ በመደበቅ ነው። ስለዚህ ለፍልስፍናው፣ ለቲዎሪው፣ ለሎጂኩ፣ ለኬሚስቲሪው ግዜ ስትሰጥ ለተግባር አምልኮት ግዜ እንዳይኖርህ አሸምቆ ይታገልሃል። ብዙ የምታውቅና ለየት ያለ የአመላለከት ዳራ እንዳለህ እንድታስብ መንገድ ይቀርጽልሃል። ከዚያ አንዴ ከውስጥ መኮፈስ ከጀመረ በኋላ በምንም ምክንያት የሌሎችን ተግሳጽና ምክር ለመቀበል እስከሚያዳግትበት ርቀት ድረስ እያንሸራተተ ያመጣሃል። አልፎም ተርፎ ቀስ በቀስ እውቀትህን ወደ መርዝነት ይቀይረዋል። ከዛ በኋላ በቃ ሌላውን የሚያድን ሳይሆን የሚያጠፋ፣ ሌላውን የሚያበረታ ሳይሆን የሚያደክም፣ ሌላውን የሚያንጽ ሳይሆን የሚያፈርስ እየሆነ ብዙ የጥፋት ግብሮችን የሚሰበስብበት የእውቀት መስመር ያደርገዋል። አሁን እንደዚህ በሚያደርግበት ግዜ አታውቀውም። እያለማህና መልካም ነገር እያሰራጨህ እንዲመስልህ ነው የሚያደርገው። በዚያ ላይ ሳይንቲስት፣ መሐንዲስ፣ ዶክተር፣ ተመራማሪ እንደሆነ ሰው ማጥፋቱን ሳያውቅ የሚያጠፋ የለም።
የጠቋርም መንፈስ የዚሁን የሲዖል መንፈስ እውቀት ውስጥ የመደበቅ ባህሪይ ሲኖረው፤ በመሠረታዊነት መንፈሳዊ እውቀት ውስጥ በመደበቅ ተመጻዳቂ፣ ሁልግዜ የሚተቾ፣ እኔ ብቻ ልደመጥ፣ እኔ የጠላሁት ይጠላ የሚልና የሚያስብል፣ መተግበር ሳይሆን መናገር የሚቀለው፣ በሌላ መንፈሳዊ ሰው መበለጥ የሚያንገበግበው፣ ሁሉንም በአንድ ግዜ ለማወቅ የሚጥር፣ ሁሉም ሰው ይደግፈኝ ይወደደኝ የሚል፣ እኔ ካላመንኩበት አይሠራም የሚል፣ ክርክርና ጭቅጭቅ የሚቀናው፣ ወደሌሎች ሰዎች ሕፀፅ ዘወትር መጠቆም የሚቀናው፣ እውነትን እያየ እንኳን ለመቀበል የማያምን፣ እርሱ ካለው እውቀት ውጪ ትክክል እንኳን ቢሆን ለማዳመጥ ግዜ የማይሰጥ አገልጋይ አድርጎት ቁጭ ይላል። የነዚህን ሰዎች እውቀትና ብዙዎችን የመሳብ ችሎታ ስለሚፈልገው ተለቅ ባለ የሥልጣን ደረጃ አሊያ የዝና ካብ ላይ በማስቀመጥ ብዙ ከስር ያሉ የተዋረድ ሰዎችን ለማጥፋት ይጠቀምባቸዋል።

መናፍስት ላይ ንቁ።
#ጸባኦት_ይከተላችሁ
@abat_memhir_girma

## ✝ የመናፍስት መደበቅ ✝
## ክፍል 3•

በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ አሜን።

ቅዱስ የሆንክ ጌታ አባት ሆይ፤ የተገኘንበትን ሰዓት ግዜ ባርክልን። በመለኮታዊ ኃይልህ ሕይወታችንን ሁሉ ቀድሰው። በምስጋና እና በቅዱሱ ቦታ ላይ አቁመን። ውስጣዊ ጠባያቶቻችንና የኑሮአችንን አቀጣጫ ሰላምና በረከት ስጣቸው። በመውጣት በመግባታችን መካከል ሊሳተፉ የሚወዱ ርኩሳን መናፍስትን አስወግድልን። የጥቃት ኃይላቸውንና ስውር ግብራቸውን የምንከላከልበትን የሃይማኖት ጋሻ ስጠን። ሰማያዊ ቃልኪዳንህ እና ምሪት ከብርሃንህ ጋር ከሕይወታችን እንዲገኙ ቀኝ እጅህን ስደድልን። አገራችንን እና ሕዝቦቿን በቅዱስ መንፈስህ ጠብቅልን። በቅዱስ ልጅህ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም። በቅድስት እናትህ እመቤታችን ድንግል ማርያም ስም። አሜን

✟✟✟

## ✝ ልማድና ባህሪይ ውስጥ የሚደበቁ መናፍስት ✝

ልማድና ባህሪይ ውስጥ የሚደበቁ መናፍስት የአብዛኛው ሰው መሠረታዊ ችግር ናቸው። መንፈስ ተፈጥሮአዊ አቋሙ የማይታይ የማይጨበጥ ነውና፤ ባህሪያችን ውስጥ በሚደበቅበት ግዜ ባህሪያችንን ነው የሚመስለው። ልማዳችንን ሲለምደው ልማዳችንን ሆኖ ነው የሚቀመጠው። ጥቁር ቀለም ላይ ጥቁር ቀለም ጠብ ስታደርጉ እንዴት ነው? የመንፈስም ባህሪይ ይኸው ነው። ውስጣዊ ሕይወትህ ውስጥ በሚደበቅበት ግዜ የአኗኗርህን መልክና ሁኔታ መስሎ ነው የሚያደፍጠው። ስለዚህ ስለመመሸጉና ስለማድፈጡ ፍንጭ እንዳይሰጥ አድርጎ በሚያመቸው ቦታ ላይ ሄዶ ይደበቃል።

✟✟✟

አንደኛው የመንፈስ ምቹ መደበቂያና ማድፈጫ ቦታ <u>ልማድና ባህሪያችን</u> ነው። በጣም አስቸጋሪውና የብዙ ሰው ፈተና የሚሆነውም በጠባያቶቻችን ውስጥ የገባ መንፈስ ጠባያችንን ሲለምደው ነው።
መናፍስት ሁልግዜ የሚደበቁበት ቦታ <u>ያልተቀደሰው ስፍራ</u> ላይ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስና ኃይል የሌለው ቦታ ላይ ነው። እነሆም ባህሪያችን ውስጥ ሰማያዊ ሕይወትንና የሃይማኖት ገጽታን የማይወክል ጠባይና ልማድ ካለ፤ እዛ ባህሪይ ውስጥ ተደብቆ በሚፈልገው መልኩ የሚያበልጽገውና የሚጠቀምበት ምሽጉ ይሆናል።

✟✟✟

ከባህሪይ አንፃር የተመለከትን ከሆነ አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሮ ባህሪያቸው ትዕግስት የለሽ ችኩል ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ አይነት ባህሪይ እንዳለን መንፈሱ ውስጣዊ ሕይወታችንንና የኑሮ አቅጣጫችንን አንብቦ ከተመለከተ፤ ይኸው ባህሪያችን ውስጥ ባህሪይ ሆኖ ይቀመጣል። ከዚያም ይህንን ያደፈጠበትን ባህሪይ በሚፈልገው መልኩና የጥፋት አካሄድ ወደራሱ የሴራ መንገድ ይቀርጸዋል። ለምሳሌ ጸሎትና ስግደት በምናደርግበት ግዜ ለእግዚአብሔር መልስና ጸጋ ችኩል እንድሆን ስልት ይቀይሳል። ልክ የእግዚአብሔር ግዜ እኛ ላይ እንደዘገየ አድርጎ ዙሪያችንን ስለሚያሳየን የኛ ጸሎትና ስግደት ወደ ፈጣሪ እንደማይደርስ እንድናምን ሚስጢራዊ ጥበቦችን ይጠቀማል። አብረውን የሚጸልዩ ሰዎች ከኛ የተሻለ ደስተኛና በቶሎ

ከአምላክ መልስ እንደሚቀበሉ አስመስሎ ያሳየናል። አሳብንና ምናብን የመቆጣጠር ችሎታው እንደ ዓይነጥላ ላሉ መናፍስት ቀላል ስለሆነ፤ ችግር የለበትም። ከዛ በኋላ አንተ ቀድሞውኑም በባህሪይ ችኩል ነህና፤ ቸኩለህ ተስፋ እንድትቆርጥ ይህንን ባህሪይህን ያበለጽገዋል። አሳማኝ ምክንያቶችን ከውስጥህ እየደረደረ መስገድና መጸለይ እንድታቆም ይገፋሃል። ባህሪይ ውስጥ ባህሪይ ሆኖ ነውና ያለው ራስህን ያዳመጥክ እየመሰለክ ገና ጸሎት ሳትጀምር ይደክምሃል። መስገድ ሳትጀምር ያደበዝዝሃል። ለቀናት እያዘገየ ይሄንን የአእምሮና የአካል ድክመት ያለማምድሃል። ከዛ ለሳምንት ያደክመሃል። ለወራት ያደክምሃል። በቃ ቀስ በቀስ ከጸሎትና ከስግደት ሕይወት ደክመህ ውስጥህን እየቆለፈ እየቆለፈ ያርቅሃል።

በሌላውም ከዚህ ትእግስት አጥ በሆነ ባህሪያችን ውስጥ በሚደበቅበት ግዜ፤ ሰዓቱን በማዛባት በምናባችን ውስጥ እንድንደክም ልባችንን ይጎትተዋል። ይሄ ምን ማለት ነው የጸሎት ሰዓት ከመድረሱ በፊት ግዜያቱን የፈጠነ እንዲመስለን ያደርገዋል። በተቃራኒው ደግሞ ጸሎት ስንጀምር ሰዓቱ የተጎተተ እንዲመስለን በማድረግ ሕሊናችንን ስለሚጫነው ከችኩልነታችን ውስጥ ሆኖ ቶሎ እንድንደክም የማደንበኸ ገጽታን ለሰውነታችን ያለብሰዋል። በዚህ ምክንያት ገና ጸሎት ስታስብ እየደከመህ ከአምልኮት እየተለየህ ትመጣለህ።

✞✞✞

ልማድ ውስጥ በሚያደፍጥበት በተመሳሳይ መልኩ በሚስጢር ልማድህን ሆኖ ያጠቃሃል። ለምሳሌ ብዙ ወጣቶች የወሲብ ፊልምን በመመልከት ልማድ ውስጥ ገብተው ይሰቃያሉ። በመጀመሪያ ሲጀምሩት እንዲሁ ቀላል አድርገው ይሆንና ከግዜያት  በኋላ ግን የሕይወታቸው አንዱ ክፍል ሆኖና ለመተው ከብዶ ቁጭ ይላል። ለሰው የማያዋዩት የውስጥ ደዌ ሆኖ እንደ ሱስ ይቆራኛቸዋል። የተንኮሉ ተንኮል ደግሞ በጸሎትና በስግደት ሰዓትም ያዩትን የወሲብ ፊልም ምናብ ያመጣባቸውና የሕሊና እርጋታቸውን በሚፈልገው መልኩ ይመታዋል። በቃ ከዚህ በኋላማ ጸሎት የለም። ስግደት የለም። እንደዚህ ሆኜ ከምጸልይና ከምሰግድ ቢቀርስ እያሉ የአምልኮት ልምምዱን ይተውታል። መናፍስት ልማድ ውስጥ በሚቀረቀሩበት ግዜ ያንን ልማድ ነው የሚያበለጽጉት። ብዙ ሰው የማይገባውና የሚሸወደው እዚህ ጋር ነው። ጸሎትና ስግደት በየቀኑ እያደረግን መንፈሳዊ ልምምድ ልምድ ሆኖ የሕይወታችን ክፍል መሆን ሲያቅተው፤ የተወሰነ ቀናት ያደረግነው የሱስና ተመሳሳይ ልማዶች ግን ልክፍት ሆነው ራሳቸው እንድናደርጋቸው ከውስጣችን ሲጠይቁን አንጠረጥርም። ለምንድን ነው ውስጤ ጸሎትና ስግደትን እንደሌሎች ነገራት ተነቃቅቶ የማይጠይቀኝ ብለን እዚህኛው ነጥብ ላይ አንነቃም። ስለዚህ አዚም ሆኖ የተቀመጠው ጠላት መንፈሳዊ ጉዞዎች ላይ ዳፍንት እየሆነ አስቀድሞ ሲያልፈሰፍሰን የምናስቆምበትን ንቃተ ልቦና ለመያዝ አልታደልንም።

ሌላው ሥልክ ላይ የመቆየትና ረጅም ሰዓታትን በማኅበራዊ ድረገጾች ላይ ያለምንም ፍሬያማ ጉዳይ መጣድን የለመድን ከሆነ እዚህ ልማዳችን ውስጥ መንፈስ ለማድፈጥ ይመቸዋል። አሁን በቃ ያውቅበታል። ለጸሎት ስትነሳሳ የአስተሳሰብህን ትኩረት አቅጣጫዎች ወደ እጅህ ሥልክ ላይ እንድትሰበስብ ሌሎች እይታዎችህን ስለሚያለዝባቸው፤ ምንም ቁም ነገር ሳታደርግ ግዜውን እንድትፈጀውና እንዲደብትህ አዚም ይለቃል። ስለዚህ ጸሎት ሰዓት ላይ እጅህ ከሥልክህ አልለይ ይላል። ዓይንህ የሥልክ ብርሃን ይናፍቀዋል። ሥልክህን ካልነካካህ በቀር መቀርዘዝና መፍዘዝ እንደሚሆንብህ መጀመሪያ ሕሊናህን ስለሚያሳምነው ልማድህን እንደመሣሪያ ለመጠቀም አይቸገርም። ሌሎች ተመሳሳይ ልማዶች ላይ በሚደበቅበት ግዜ ይህንኑ ድበታና ማፍዘዝ እየተጠቀመ ትኩረትህን ወደ ልማድህ እንድታደርግ በረቀቀ መናፍስታዊ ስልት ተጠቅሞ ከመንበርከክ ሕይወት እየነጠለህ እየነጠለህ ይመጣል።

በሚገርም ሁኔታ ባህሪያችን ውስጥ መንፈስ ሲደበቅ አንዳንዴ በጎ ነገራችን ውስጥ ሊያደፍጥ ይችላል። ይሄ ምን ማለት ነው ለምሳሌ፣ ይሉኝታና ሰውን ለማስቀየም የምንፈራ ከሆነ ይሄንን ጠባያችን ወደራሱ በሚመቸው መልኩ ሊጠመዝዘውና በሰዎች ይሉኝታ ሰበብ ከጸሎት ሕይወት የምንርቅበትን መንገድ ሊያመቻች ይችላል።

✞✞✞

አንዳንድ ሰዎች በባህሪያቸው ቁጡና ግልፈተኛ ሊሆኑ ይችላሉ። አሊያም አኩራፊ አይነት ጠባያት ይኖራቸው ይሆናል። ወይንም ከተጣሉት ሰዎች ጋራ ቂም የሚቋጥሩ ሰዎች ይሆናሉ። እንደነዚህ አይነት ባህሪያት ለመናፍስቱ በጣም ይመቻቸዋል። እንዴት ማለት መሰላችሁ፣ አንድ ጠረጴዛ ጽድት ብሎ ተጠርጎ ነገር ግን በጣም ትንሽም ብትሆን ቆሻሻ ብትኖር ዝንብ መጥታ ልታርፍ የምትችለው በዚያ ቦታ ላይ ነው።

መናፍስትም እንዲሁ ናቸው። በብዙ መልኩና ሁኔታዎች ላይ መልካም ጠባያቶች ቢኖሩንም፤ አንዲትም ትሁን ያፈነገጠች ጠባይና ልማድ ካለቺን፤ መናፍስቱ መጥተው እዚያች ባህሪይ ውስጥ ይመሸጋሉ። ይደበቃሉ። ቀስ በቀስም እያበለጸጉትና ባደፈጡበት ባህሪያችን በኩል ራሳችንን እንድናዳምጥ እየገፉን ሌሎቹን መልካም ባህሪያቶቻችንን ሊያጠለሹ በሥልትና በዝግታ ይሰራሉ። ይሄን ለመመልከት በፊት የነበረንን የቀደመ ባህሪይና ዛሬ ያለንን ጠባይ አንድ ቦታ አስቀምጦ ማጤን ነው።

✞✞✞

ልማድና ባህሪይ ውስጥ የሚያደፍጡትን መናፍስቶች የምንዋጋው በንስሐ እና በቅዱስ ቁርባን በኩል ነው። ከተሰወረና ከተገለጠ የባህሪይ ኃጢአቶች ለመራቅ ወደ ሥጋና ደሙ መቅረብ ያስፈልጋል። እና በቅዱስ ቁርባን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ጉዞ ማየት ስንጀምር የተሸሸገ የልማድና የባህሪይ ኃጥያትን ከሕይወታችን አርቀን፤ ነገ ከምንወልዳቸው ከልጆች ትከሻም ላይ አርቀን፤ የተሰረየና የተባረከ የሕይወት ዘመን እንዲመጣልን ምክንያት ይሆናል ማለት ነው። ኃጥያት ከተሰረየ ያየነው፤ የሰማነው ሁሉ የተባረከ ይሆናል። የምንንናገረው፤ የምንነካው ሁሉ የተባረከ ይሆናል። የሚመጡት የሕይወት ዕድሎቻችን ሁሉ የተባረኩ ይሆናሉ።

መናፍስት ላይ ንቁ።
#ጸባኦት_ይከተላችሁ
@abat_memhir_girma

## ✝ የመናፍስት መደበቅ ✝
## ክፍል 4•

### ኃጢአት ውስጥ የመናፍስት መደበቅ

መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው የሰው ልጆች ኃጢአት ብሎ የሚነግረን አዳምና ሔዋን አትንኩ የተባሉት ዕፀ በመብላታቸው እንደሆነ ነው። ከሕይወት ዛፍ ፍሬ ከበሉ በኋላ ኃጢአት ወደ ሰው ልጆች መምጣት እንደ ጀመረ በኦሪት ዘፍጥረት 3፥22 ላይ የምናገኘው ይሆናል። ቃሉን ስንመለከተው እንደዚህ ነው የሚለው።
"እግዚአብሔር አምላክም አለ። እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤"

መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ አለ እግዚአብሔር ቃል። አዳም በመጀመሪያው የተፈጥሮ ገጽታውና ኑሮው ውስጥ የሚያውቀው መልካሙን እግዚአብሔር ብቻ ነበረ። አሁን ግን የእግዚአብሔርን ሕግ ተላልፏልና፤ አስቀድሞ የእግዚአብሔርን ሕልውና ተላልፎ የነበረውን ክፉውን ዲያቢሎስ አወቀ። ኃጢአት ወደ ልቡ ገባች ማለት ነው። ጸጋና ሞገሱም ስለተገፈፈ የሰውነቱም ብርሃን ከእርሱ ተለይቶ ሲነሣ ምልክት ይሆን ዘንድ በጣቶቹ ላይ ጥፍር የምንለው ብርሃንን የሚወክል ነጣ ያለ ክፍል ለመተላለፉ ማስታወሻ ሆኖ እንዲቀር በቀለ። ከዚህም ግዜ ጀምሮ ዲያቢሎስ በመጀመሪያዋ የኃጢአት በደል በኩል ወደ ሰው ልጆች ሕይወት በቀላሉ ለመምጣትና ባላጋራ ሆኖ ለመኖር የሚችልበትን ዕድልና አጋጣሚ ስላገኘ ተጠቀመበት። ይህንን የዲያቢሎስና የሰው ልጆች መዛመድና ኃጢአት ውስጥ ተሸሽጎ የማጥቃቱን እውነታ በቃየን ሕይወት ላይ ተተርጉሞ የምናየው ነው።

✞✞✞

ቃየን እና ወንድሙ አቤል ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ሰዉ። ቃየን ከምድር ፍሬ ሲያገባ፤ አቤል ከሰቡት በጎች መካከል #በኩራት ለእግዚአብሔር አገባ። ቃየን ዐሥራት ሲያወጣ፤ አቤሎ ዐሥራት በኩራት አወጣ። ተስገብግበን እና እንደው በቃ መሆን ስላለበት ተገደን ለእግዚአብሔር የምንሰጥ ከሆነ ዐሥራት አወጣን ነው። "ይሄ ለጌታዬ፥ ስለ ፍቅሩና ስለ ቸርነቱ፤ ስለ ጥበቃውና ኃያልነቱ የሚሰጥ የአባቴ ነው" ብለህ ስትሰጥ ዐሥራቱን በኩራት አወጣህ። ዛሬ ዐሥራት የምናወጣ ብዙዎች እንሆናለን። ይኸውላችሁ እዚህ አሁን አቤል ከሰቡት መካከል መርጦ በኩራት ለእግዚአብሔር ሲሰጥ፤ እግዚአብሔር ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ። " ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም። ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ።"
(ኦሪት ዘፍጥረት 4፥5)

በአዳምና በሔዋን ግዜ ያልነበረው ፊት ማጥቆር ከየት መጣ? ልጃቸው ቃየን ተናደደ ፊቱም ጠቆረ ይላል። አዳምና ሔዋን ከገነት ተባርረው ወደ ምድር ሲመለሱ፤ በእባብ አካለ ሥጋ ተሰውሮ የነበረው ዲያቢሎስ የት ሄደ? ይሄን ጥያቄ ዛሬ ብዙዎች አይጠይቁም። እንደው ዝም ብለው ደረቅ ቃሉን ሰምተውና አሰምተው፤ ከገነት ለመውጣታቸን ምክንያት የሆነው ጠላት ወደ የት ሄደ የሚለው ላይ ትኩረት ሳይሰጡ ዕድሜያቸው ሄደ። ዘመናቸው ሄደ። ትውልዳቸው ሄደ። አዳምና ሔዋን ብቻ አልነበሩም ከገነት የወጡት። ዲያቢሎሱም ቀደምት እርግማኑ ላይ እርግማን ጨምሮ ተከትሎዋቸዋል። ክፋትን ያውቁ ዘንድ በተከፈተ አዲሱ ልባቸውም በኩል የራሱን ቦታና ይዞታ ማግኘት ስለቻለ በዘራቸው ውስጥ ገብቶ እግዚአብሔር የገባላቸውን ቃልኪዳን እንዳያገኙ ገና ከማሳጸን ጀምሮ አብሮ እየተወለደ፤ ለሰው ልጆች ክፋትንና እርግማንን ማወራረስ ጀመረ። የቃየንም መወለድ ውስጥ ዘር አጋንንት ነበረችና ወደ እግዚአብሔር የኩራት መሥዋዕት ባገባው አቤል ላይ ተናደደች። በእርሷ ከውስጥ መበሳጨትም የቃየን መልክ ከውጪ ጠቆረ።

✞✞✞

ተወራርሳ ከቃየን ባህሪይ ውስጥ ባህሪይ ሆና ያለቺውን አጋንንት እግዚአብሔር አያትና ለቃየን እንዲህ አለው። "እግዚአብሔርም ቃየንን አለው። ለምን ተናደድህ? ለምንስ ፊትህ ጠቆረ? መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን #ኃጢአት_በደጅ _ታደባለች፤ #ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፥ አንተ ግን #በእርስዋ_ንገሥባት።"

<< ኃጢአት በደጅህ ታደባለች፣ ፈቃድዋም፣ በእርስዋ ንገሥባት >> የሚሉት ቃላት በሴት ጾታ መገለጻቸው፤ በቃየን ሕይወት ውስጥ ኃጢአት ሆና ያደፈጠች አጋንንት መኖሯን ይነግረናል። ይህቺ ዘር አጋንንትም የቃየንን ወስጣዊ ልቦና እና

የወንድማዊነት ፍቅር አዷንዝዛ የአቤልን ደም በሜዳ ጠጥታለች። በእርስዋ ንገሥባት ያለው የእግዚአብሔር አምላክ የማሽነፊያ ድምፅ በቃየን ኑሮ ውስጥ ተለውጦ ደም በማፍሰስ ኃጢአት እና የመጀመሪያውን ግዲያ በማስፈጸም ወንጀል ከሰሰቺው።

✞✞✞

መናፍስት በኃጢአት ውስጥ የመደበቃቸው ትልቁ ምክንያትና ፍላጎት ይሄ ነው። በበደል ሥራ በወንጀል ድርጊት ዘንድ ፈጣሪ ፊት ለመክሰስ እንዲችሉ ኃጢአት ውስጥ መናፍስት ይደበቃሉ። ኃጢአት በደጅህ ታደባለች የሚለው ቃል ውስጥ፤ ታደባለች በማለት የቃየን ሕይወት ውስጥ ለመደበቅና ተሰውራ የጥፋት ግብርን ለመፈጸም የምትፈልግ አጥቂ መኖሯን እግዚአብሔር ለቃየን ነግሮታል። የቃየንን ሕይወትና ዘመን ለመክሰስና ለማጥፋት #የምትፈለግ ስለመሆኗም ፈቃድዋ በአንተ ላይ ነው በማለት ነግሮታል። ያለውም አልቀረ በወንድሙ ላይ እንዲነሣሣ በማድረግ የአቤል ደም ክስ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር እንዲጮኽ ሆኗል።

✞✞✞

ዛሬም ከብዙ የግፍ ስራዎች፣ የእልቂት ዜናዎች፣ የትዕቢት ድምፆች፣ የዋይታና ሰቆቃ ግዜዎች፣ የመጠፋፋት ታሪኮች፣ አንዱ በአንዱ ላይ የመነሣት ኃጢአቶች ውስጥ ተደብቀው የሚከሱ መናፍስት በሕይወታችን ውስጥ አሉ። የዲያቢሎስ ዓላማና ራእይ ኃጢአት መሥራት አይደለም። የጉዞውን መጨረሻ ያረጋገጠው ሰይጣን ኃጢአትን ቢሠራ ባይሠራ ለእርሱ የሚጨምረው አሊያ የሚቀንስ የለውም። የዲያብሎስ ፍላጎት በእርሱ ፋንታ ተተክተው የእግዚአብሔር ክብር ለመውረስ የተመረጡትን የሰው ልጆችን ኃጢአት በማሠራት የሰው ልጆችን ጸጋና የአምላክን ክብር ወራሽነታቸውን በመግፈፍ፤ በመቀጠል ባሠራው የኃጢአት መዝገብ መሠረት የክስ ፋይል በመክፈት፤ በዘላለማዊ የፍርድ ውሳኔ በኩል ተያይዞ መጥፋት ነው። የራእዩን ቃል በምዕራፍ ዐሥራ ሁለት ቁጥር ዐሥር የሚነግረን ይሄንን ነው። "የወንድሞቻችን #<u>ከሳሽ ወደ ምድር ተጥሎአልና</u>" ነው የሚለው።

ከመጀመሪያው ከሰማይ ከተጣለበት ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ባለው የዘመናት ጉዞ ውስጥ ሰይጣንና ሠራዊቱ በተለያየ መንገድ የሰው ልጆችን ከመነሻው ትውልድ አስጀምሮ እስከ መጨረሻው የምጽዕት ቀን ፍጻሜ ድረስ ሕልውናቸውና የመኖር ጥያቄያቸው ውስጥ እየገባ እያጨነገፈ ይገኛል፡ ይቀጥልማል። ይህ የዲያቢሎስ ስነ ተፈጥሮው አንዱ እንድምታ ነው። የወንድሞቻችን ከሳሽ የተባለውም ለዚሁ ነው። ከመክሰሱ አያቋርጥም። ከምቀኝነቱ አይለዝብም። ከክፋቱ አይቆጠብም። ከውሸቱና አመፃው አይስታጎልም። ወደ ምድር የተጣለው ሊከስ ነው። በኃጢአት ሊከስህ፣ በክፋት ሊከስህ፣ በአመፃ ሊከስህ፣ በዝሙት ሊከስህ፣ በምቀኝነት ሊከስህ፣ በትዕቢትና በግፍ ሊከስህ፣ በስድብና በማንጓጠጥ ድምፅህ ሊከስህ፣ በደም ማፍሰስ ሊከስህ፣ በመቃወም ሊከስህ፣ በደዌ ሊከስህ፣ በችግርና ሰላም በማጣት ጦርነትና የእርስ በእርስ ፍጅት ሊከስህ ነው የተጣለው።

ዛሬ በተገኘንበት ዘመን እጅግ የበዙ ክርስቲያኖች ወደ ንስሐ ለመቅረብ አልቻሉም። <u>ይፈራሉ</u>፣ <u>ይሸሻሉ</u>፣ <u>ይደበቃሉ</u>። ይሄ ለምን ሆነ? እንዴት ወደ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ያሸሽናል? ኃጢአትን ሸሽጎ በክፋት ድበቃ ውስጥ መገኘት እንዴት መርጥን? ለዚህ ምክንያቱ በደጃችን ኃጢአት ውስጥ ያደባ ጠላት ስላለብን ነው። ይኸው እዚህ ጋር እንኳን እኮ አንነቃም። የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅና በደሉን ለማስተሰረይ ለምን ይፈራል? ብለን እንኳን አንጠረጥርም። የምንፈራው እኛ አይደለንም። <u>ኃጢአት ውስጥ የተደበቀው አጋንንት ምሽጉ ሊነሣበት</u> ስለሆነ ነው የሚፈራው። ስለዚህ በተለያየ ምክንያት ከኃጢአት አረንቋና የበደል ዘመን እስራት

ውስጥ እንድንቆይ በስልትና በጥበብ ይፈትናል።

✞✞✞

ንስሐ መግባት ኃጢአትን ብቻ አይደለም የሚያጥበው። ኃጢአት ውስጥ ያደባ መንፈስን ይጠርጋል። ይህንን አባቶች አይስተምሩም። መምህራኑ አይሰብኩትም። ለምን እንደሆነ አይታወቅም ግን ሕብረተሰብ ውስጥ ሕብረት ፈጥሮ ያለውን ጠላት ለማስቆም የሚደረገው መንፈሳዊ ትንንቅ ላይ ብዙዎች የሚያሳዩት አቋም የላሸቀና ሃይማኖታዊ እይታ የተጥበረበረ ነው። በብዙ የስብከት ቋንቋዎች ላይ የአገልግሎቱ መዳረሻ መልእክት ንስሐ ግቡ የሚል ነው። ምዕመኑ ግን ንስሐ እንዳይገባ አስቀድሞ ወደ ሕይወቱ ተደብቀው የገቡ መናፍስት እያሉ እንዴት ይሆናል? ዕድልን አጨንግፎ የያዘ የዓይነጥላ መንፈስ እያለብን ንስሐ ለመግባት እንዴት በቀላሉ እንችላለን? ይሄ በአገልግሎቱ በኩል ለተሰለፉት የሚቀረብ መሠረታዊ ጥያቄ ይሆናል። ኃጢአት ውስጥ የተደበቁ መናፍስትን ለማስቆም <u>ንስሐ መግባትና በቅዱስ ቁርባን በኩል መቀደስ ግድ ነው።</u>

✞✞✞

መናፍስት ላይ ንቁ
#ጸባኦት_ይከተላችሁ
@abat_memhir_girma

## <u>✝ የመናፍስት መደበቅ ✝</u>
## <u>ክፍል 5•</u>

አቤቱ የሠራዊት አለቃ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ሆይ፣ እስከዚህችም ሰዓት ስላደረሥከን እናመሰግንሃለን። ቀሪ ግዜያችንን ትባርክልን ዘንድ እንለምንሃለን። የሰው ልጆችን ውደቀትና ጉዳት ተመልክተህ ከሰማያዊ መንበርህ ወርደህ ባህሪያቶቻችን የተካፈልክ ቅዱስ ጌታ ሆይ፣ ቃልኪዳህንና በረከትህን ስጠን። ሰማያዊ ቃልህንና ሞገስህን ለሕይወታችን አካፍለን። በአህያይቱ ውርጫ ሆነህ ወደ ኢየሩሳሌም የገባህ ጌታ ሆይ፣ ከኛም ሕይወት ጋር ሆነህ ወደ ሰማያዊት አገርህ ኢየሩሳሌም ትወስደን ዘንድ በቅድስት እናታችን እመቤታችን ድንግል ማርያም ስም እንለምናለን። ዘመናችንን ሁሉ ትቀድስልን ዘንድ፣ ርኩሳን መናፍስትንም ከኑሮአችን ውስጥ ታስወግድልን ዘንድ በሊቃነ መልአክትህ ስም እንማጸናለን። አገራችንንና ሕዝቢችን በመለኮታዊ ጥበቃህና ኃይል ትጠብቃት ዘንድ ፍቃድህ ይሁን። በቅዱስ ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

### <u>✝ የቤተሰብ ልማድና ባህሪይ ውስጥ የመናፍስት መደበቅ ✝</u>

በክፍል ሁለት ቆይታችን መናፍስት በራሳችን ልማድና ባህሪይ ውስጥ እንደሚደበቁ አይተናል። አሁን እዚህ የምንመለከተው ደግሞ በቤተሰብ አሊያም በምንኖርበት ስፍራ ባሉ ሰዎች ውስጥ የመናፍስት መደበቅን የተመለከተ ይሆናል።

✞✞✞

የአምልኮት ሕይወትን እንደጀመርን ዕለት ዕለት በስግደትና በጸሎት እየተገኘን በመንፈሳዊ መዋቅር ውስጥ ያለን ጸጋና ሞገስ እያደገና እየበረታን በምንመጣበት ግዜ ውስጥ በመጀመሪያው ክፍል አሊያም ሰማያዊ ልምምዱን ጀምረን ከቆየን በኋላ አንዱ መናፍስት የፈተና ማእበል የሚያስነሱት ቅርባችን ባሉ ሰዎች በኩል

የሚያገኙትን ክፍተት በመጠቀም ነው። እነዚህ ሰዎች አብረው የሚኖሩ ወላጆች፣ እህት ወንድሞች፣ ዘመዶች አሊያም ጓደኞች ሊሆኑ ይችላሉ። አሁን በጣም እርግጠኛ ነኝ መንፈሳዊ ልምምድ ከጀመራችሁ በኋላ ከብዙ የቅርብ ሰዎች ጋር መግባባትና አንድ ሰላማዊ ምዕራፍ ላይ ተስማምታችሁ መድረስ ያቃታችሁ ሰዎች ጥቂቶች አይደላችሁም።

✝✝✝

ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ ከሰይጣን እንርቃለን። ወደማን ስንቀርብ? ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ። ወደ ሰማያዊው አባት በምድር ሕይወታችን መቀረብ ስንጀምር ታዲያ ወደ ዓለም የቀረቡ ሰዎች ይርቁናል አሊያም እኛ እንርቃቸዋለን። ይሄ ለምን ይሆናል? ብለን በመንፈሳዊ እይታ በኩል ስንመረምር የሚርቁን የቅርብ ሰዎቻችን ሳይሆኑ <u>የቅርብ ሰዎቻችን ውስጥ ያሉት መናፍስት ናቸው</u>። በዙሪያችን ያሉት ሰዎች በአምልኮት በኩል ስለሚመጣው መንፈሳዊ ንቃትና ስለ ርኩሳን ጠላቶች ያላቸው ግንዛቤ ደብዛዛ ከሆነ ባህሪይና ልማዳቸው ውስጥ ለመጠቀም መንፈሱ ምንም አይቸገርም። እነዚህ የቅርብ ሰዎቻችን አስቀድሞ ቶሎ የመነጫነጭ እና የማኩረፍ ጠባያቶች ከነበሯቸው፤ ስግደትና ጸሎት ከጀመርን በኋላ በረባው ባልረባው ሊነዘንዙንና ሳናጠፋም አጥፍተንም የከበደ ኩርፊያ ሊያኮርፉን ይችላሉ። በቀላሉ ልንፈታቸው የሚገቡ የዕለት ተዕለት ግጭቶች ከአምልኮት በኋላ መልክና ይዘታቸውን ሳይቀይሩ በጫናቸው ግን የከፋ ሆነው ድክም እስክንል ድረስ ልንጨቃጨቅባቸው እና ልንጣላባቸው እንችላለን። በተለይ በተለይ በአንድ ቤት ጣሪያ ስር አብረውን የሚኖሩ ሰዎች አመላቸውና ሁኔታቸው አልመች እያለን፤ በተበጠበጠ አእምሮና በተረበሸ መንፈስ ውስጥ እንድንቆይ በተለያዩ ግዜያት የተለያዩ ስልቶችን እየተጠቀመ በመፈተን ከመንፈሳዊ ልምምዳችን እንድንርቅ ይታገላል።

✝✝✝

በአንድ ቤትና አከባቢ አብራችሁ የምትኖሩ ሰዎች በጋራ ለጸሎትና ለስግደት በርቱ የምለው ለዚህ ነው። በተለይ የዓይነጥላና የመተት መናፍስት ከአንድ ሰው ወደ አንድ ሰው የመዘዋወር አቅማቸው በጣም ከፍተኛ ነው። ቡዳ ሆነው በቀላሉ ይወራረሳሉ። አሁን ከቤተሰቡ አባል መካከል አንዱ በሚጸልይበት ግዜ መናፍስቱ ይነሱ እና ወደሌላ ወደማይጸልየው ሰው ሄደው ይደበቃሉ። ሰው ላይ ብቻ ሳይሆን ግዑዝ ነገራትም ላይ ሊደበቅ ይችላል። አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ። #በጸሎት ቤት በርትታ የምትጸልይ አንድ ሴት፤ ሁልግዜ ወደ ጸሎት ቤት ገብታ መንበርከክ ከጀመረች በኋላ ሽንት ቤት እንድትሄድ ሁሌ ይገፋፋታል። ሆዷንም አጥብቆ ስለሚያስጨንቃት አንዳንዴ ጸሎት አቋርጣ ትወጣለች። በዚህ ልምምድ ውስጥ ከቆየች በኋላ አንድ ወቀት ላይ መንፈሱ ሲጋለጥ ምን አለ "ሽንት ሄዳ ተጠቅማ በተመለሰች ቁጥር እኔ ሶፍት ላይ አሊያም እዛው ሽንት ቤት እቀመጣለሁ፤ ከዛ ራሷ ሄዳ ትሰግዳለች" አለ። ይኸውላችሁ እንግዲህ አንዱ ስልቱ እንደዚህ ነው። ጸሎት ለማቋረጥና ከስግደት ለመሸሽ የማይዘይደው መንገድ የለም። ይሄ አካሄዱ በሰዎችም ላይ ሲሆን፤ እኛ ወደ ጸሎት ስንገባ ተነስቶ ወደ ቅርብ ሰዎች ሄዶ ይደበቃል። ጸሎት ላይ በርትተን የሆነ እንደሆነ መጋለጡ የማይቀር እንደሆነ ስለሚያውቅ የሚሰወርበትን ምሽግ ይፈልጋል። ያ ደግሞ በተቀዳሚነት ጸሎትና ስግደት የማያውቅ ልብና ሰውነት ነው።
#ዓረብ አገር ያለች አንድ እህታችንም እንዳጫወተቺኝ፤ የዕለቱን ሥራ ጨርሳ፣ የሚሚላውን አሟልታና ግዜ አግኝታ ልክ ጸሎት ልትገባ ስትል የቤቱ እመቤት መጥታ እንደምትረብሻት ነግራኛለች። መስገድና መጸለይ ሳትጀምር በፊት በራሷ የእረፍት ግዜ ዝር ብላ የማታውቀው ሴት፤ የአምልኮት ሕይወተ ጥላ ውስጥ ማረፍ ስትጀምር መጥታ እንደምትበጠብጣት ተገርማ ነው የነገረቺኝ።
በሌላም በኩል መንፈሱ የቅርብ ሰውን በማሰመምና የአእምሮ ጭንቀት በመፍጠር

የኛን የጸሎት ግዜና ሕይወት ለማስነፍ አቅጣጫ ሊቀይስና ሊያስታጉለን ይችላል።

✟✟✟

በቤተሰብ ውስጥ የመደበቅና አሸምቆ የማጥቃትን መናፍስታዊ አካሄድ ጠላት በስልታዊ የጥፋት አሠራርና የማውደም ሂደት ጉዞ ውስጥ የትውልድን የተፈጥርአዊ አመሠራረት በጣም በሩቅ ተጉዞ ተጠቅሞበታል። ለዛም ይመስላል ትውልዳችን ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ ከዘመን ወደ ዘመን እየተሸጋገረ በሄደ ቁጥር አዘቅት ውስጥ እየተዘፈቀ የመጣው።

መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን የዲያቢሎስን የውስጥ ለውስጥ ሽምቅ ውጊያ በተገባ ስላወቀልን ነው በሰው ትውልድ መካከል አቋርጦ የመጣው። የማቴዎስ ወንጌልን ብትመለከቱ የብዙሃን አባት ከተባለው ብፁዕ አብርሃም ጀምሮ እስከ ቅድስት ድንግል ማርያም ያለውን የትውልድ ሰንሰለት በተዋረዱ እየጠቀሰ ያስረዳል። መባረክና መቀ'ደስ የጀመርነው ከአብርሃም ትውልድ መመሠረት ውስጥ ነው። የአብርሃም ትውልድ የነ ንጉሥ ዳዊትን ትውልድ አስገኘ። የነዳዊትም ትውልድ እነሰላትያልን አስገኘ። የነሰላትያልም ትውልድ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቤዛዊት ዓለምን አስገኘ። እመቤታችንም ጌታችንን አስገኘች። <u>እኛ ዛሬ ምን አስገኘን</u>? <u>ከኛ የተገኙ ልጆች ምን ሆኑ?</u> ብለን ስንጠይቅ አስቸጋሪ ነው።

መለሰ ብለን የቤተሰባችንን አኗኗር፣ ጤና፣ በረከት፣ ሰላም፣ ደስታ፣ ዕድል፣ ሐብት፣ እውቀት፣ ሞገስና ክብር ስንፈትሽ በእያንዳንዳችን ቤተሰብ ውስጥ ዘርፉ የተለያየ ችግር መካከል መውደቃችንን የማንካካደው ሃቅ ነው። አንዳንዶቻችን ቤተሰቦቻችን ጤና የላቸውም። የአብዛኞቻችን እናቶች በረከት ካጡ ቆይተዋል። የአንዳንዶቻችን አባቶች ሰላምና ደስታ ርቋቸው በጭንቀትና በሀዘን ተውጠው ይዳክራሉ። የሌሎቻችን ወንድሞችና እህቶች ትዳር አልሆን ብሏቸው፣ ገንዘብ አልበረከት ብሏቸው፣ ብዙ እህቶቻችን በአንክርት ኃይል በየዓረብ አገራቱ ተሰደው ወድቀው፣ ወንድሞቻችን በየበረሃው ቀልጠውና ታርደው፣ እውቀትና ገበያን እናገኛለን ብለን ደፍረን የገባንባቸው ድጦች ወደ ባሰው ማጦች አሸጋግረውን ይኸው እንሰቃያለን። የእያንዳንዳችንን የቤተሰብ ገመና ከውስጥ እናውቀዋለን። ሥራና ትምህርት ቦታ ስንገናኝ ላይ ላዩን ደስተኛ ለመምሰል በይስሙላ እንስቃለን እንጫወታለን እንጂ ወደ ውስጣችን ጠልቀን ስንመረምር በጣም የምናሳዝን የሆነ ሰንካላ መስመር ላይ የተገኘን ተሰቃዮች መሆናችንን የራሳችን ሕይወት ማስረጃ ሆኖብን የምንቀበለው እውነታ መሆኑን እንገነዘባለን።

✟✟✟

መናፍስት በቤተሰብ አባላት ላይ በሚያደፍጡበት ግዜ መደማመጥ የሚባለው የመስማማት መስፈርት ቦታውን ለመጨቃጨቅ ይተዋል። አንድ ቋንቋ እየተነጋገርን ሁለት ድምፆቻችን ጆሮዎቻችን የሚቀበሉ እስከሚመስሉ ድረስ መግባባት ያቅተናል። በተለይ በሃይማኖታዊ ጭብጦችና የእምነት እውነታዎች ላይ ተነጋግረን ወደ አንድ ውሳኔ ለመድረስ በምንም መልኩ አልቻልንም። በብዙ ዓለማዊ ከንውኖችና ሥጋዊ አካሄዶች ውስጥ ከፊት እየቀደሙ ሲመሩን የቆዩት ወላጆቻችንና ዘመዶቻችን፤ በአምልኮት ሕይወት በኩል ግን የማያዳምጡ፣ ለመስገድና ለመጸለይ በፍጹም ማሰብም የማይፈልጉ፣ የዲያቢሎስ ውጊያ ላይ ያለውን ግንዛቤ ለመረዳት ፍቃድ ያጡ እየሆኑ ያስጨነቁን ብዙዎች እንኖራለን። የዚህ ምክንያቱ ቀድመው በባህሪና በልማዳቸው ውስጥ ባሉ ጠባይና አመል ሆነው የተቀመጡ መናፍስት የማስተዋልን አዕፁቅ በማጥበባቸው ምክንያት ነው። ስለዚህ በምንም መልኩ የማያዳምጡ፣ መንፈሳዊ በጎ ነገርን ላለመቀበል ምክንያት የማያጡ፣ በሥጋዊ ልማዶችና ትርምሶች ላይ የሚነቃቁ ሆነው የመገኘታቸው ጉዳይ በእውነት ምንም የሚደንቅ አይደለም።

✞✞✞

በቤተሰብና በዙሪያ ያሉ መናፍስትን ለማሸነፍ ምን እናድርግ? ወደሚለው ስንመጣ በመጀመሪያው በራሳችን ውስጥ ያደፈጡ መናፍስትን እያሸነፍን መሄድ የግድ ነው። የማትሰግድና የማትጸልይ ሆነህ የራስህን መንፈስ ማዳከም ሳትችል፤ የቤተሰቦቼንና ዘመዶቼን ላሸንፍ ዘበት ነው። ስለዚህ አስቀድሞ ስግደትና ጸሎት የምናውቅ ሰዎች መሆን ያስፈልገናል። ሁለተኛው በራሳችን የምስጋና እና የአምልኮት ግዜ ውስጥ አብረን የቤተሰቡን መናፍስት ማሰር ይቻላል። ይሄ የእምነትና በአምላክ ክንድ ውስጥ የመገኘት መንፈሳዊ ኃይል እንጂ በላብራቶሪ ስሌቶች በቁጥሮች ቀመር የምንደርስበት ውጤት አይደለም። አንድ እህት ሁልግዜ ጸሎት በገባች ቁጥር የቤተሰቡን መናፍስት ሁሉ ስም ስማቸውን እየጠራች በውስጣቸው ያሉ መናፍስት እንዲታሠሩ በርትታ ትጸልይ ነበር። በሆነ ወቅትም መንፈሱ በተጋለጠ ግዜ በጣም እየተቆጨ የተናገረው ይሄን ነው። "እንዳለ ከያለንበት ሁሉ ጠርቃቅማ አሥራን ምን ማድረግ አቃተን!" ነበረ ያለው። በተለይ በቅዱስ ቁርባን ታትማችሁ የጸና የአምልኮት መልክ ካላችሁ ቤተሰብ ውስጥ ያደፈጡ መናፍስትን መቆጣጠር በጣም ቀላል ነው። " <u>ነገር ግን ቃል ብቻ ተናገር፥ ብላቴናዬም ይፈወሳል</u>።"
(የማቴዎስ ወንጌል 8፥8)

መናፍስት ላይ ንቁ
#ጸባኦት_ይከተላችሁ
@abat_memhir_girma

## <u>✝ የመናፍስት መደበቅ ✝</u>
## <u>ክፍል 6•</u>

አቤቱ የሠራዊት አለቃ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ሆይ፥ እስከዚህችም ሰዓት ስላደረሥከን እናመሰግንሃለን። ቀሪ ግዜያችንን ትባርክልን ዘንድ እንለምንሃለን። የሰው ልጆችን ውደቀትና ጉዳት ተመልክተህ ከሰማያዊ መንበርህ ወርደህ ባህሪያቶቻችን የተካፈልክ ቅዱስ ጌታ ሆይ፥ ቃልኪዳህንና በረከትህን ስጠን። ሰማያዊ ቃልህንና ሞገስህን ለሕይወታችን አካፍለን። በአህያይቱ ውርጫ ሆነህ ወደ ኢየሩሳሌም የገባህ ጌታ ሆይ፥ ከኛም ሕይወት ጋር ሆነህ ወደ ሰማያዊት አገርህ ኢየሩሳሌም ትወስደን ዘንድ በቅድስት እናታችን እመቤታችን ድንግል ማርያም ስም እንለምናለን። ዘመናችንን ሁሉ ትቀድስልን ዘንድ፣ ርኩሳን መናፍስትንም ከኑሮአችን ውስጥ ታስወግድልን ዘንድ በሊቃነ መልአክትህ ስም እንማጸናለን። አገራችንንና ሕዝቧችን በመለኮታዊ ጥበቃህና ኃይል ትጠብቃት ዘንድ ፍቀድ። በቅዱስ ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም።
አሜን።

### <u>✞ አከባቢና የአጋጣሚ ችግሮች ውስጥ የሚያደፍጡ መናፍስት ✞</u>

የመጨረሻው የመናፍስት መደበቅ ክፍላችን ላይ በአካባቢ(በዙሪያችን ቦታ) ላይ ስለሚያደፍጡ መናፍስትና እንዴት ከአምልኮት ሕይወት ሊያናጥቡን እንደሚሞክሩ እንመለከታለን።

✞✞✞

በ1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 5፥8 ላይ "ባላጋራችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ በዙሪያችሁ ይዞራል" የሚለው ቃል ይህንን በአከባቢ ውስጥ ስለሚዞሩ መናፍስት ይነግረናል። በሰፈርና በመኖሪያችን ዙሪያ የሚኖሩ መናፍስት

ይኖራሉ። በአንድ ወቅት አንድ ወንድም ላይ ያደፈጠ ዓይነ ጥላ ሲለፈልፍ "በቃ ሰፈር ውስጥ ቁጭ ብዬ ነበረ፤ በኋላ ሰውየው በኛ አቅጣጫ በኩል ሲያልፍ አየነው፤ እስቲ እንዴት ነው ተከትዬው ወደ ሕይወቱ መጣሁ" አለ። ከዚህ እውነታ አንፃር ዛሬ ላለነው ለዓለም ትውልዶች ሦስት ሰከንድ መንፈሳዊ ዓይን ቢሰጠን ኑሮ፤ ዓለም ላይ ሲሆን የሚታየው ሁሉ ፍጹም የተለየ መልክና ቅርጽ ይኖረው ነበረ። በምድር ላይ የተጣሉት መናፍስት በአከባቢያችን ምን ያህል ብዙ ሆነው እንደሚገኙ በመንፈሳዊ መንጽር ብንመለከታቸው ኖሮ ከጸሎት ቤታችን አሊያም ከቤተክርስቲያን አልወጣም እንል ነበረ። ለስግደትና ለጸሎት መጨቅጨቅ እስኪመስል ድረስ አንለመንም ነበረ።

✞✞✞

በተደጋጋሚ እንደተማርነው መንፈስ የሚታይ፣ የሚዳሰስና የሚጨበጥ አይደለምና በሥጋዊ እይታና አቋም በኩል ልናውቀው በምንም መልኩ አንችልም። ፍንጩን ወይንም ምልክቱን እንጂ መንፈሱን ያለ መንፈሳዊ ገጽታና ልምምድ ልንደርስበት አንችልም። ስለዚህ በአከባቢያችን፣ በሥራ ቦታችን፣ በትምህርት ቤታችን እና ወዘተ.. የመሳሰሉት ቦታዎች ላይ አርፈው ሰው ሊያጠምዱ የሚዞሩትን መናፍስት ልናውቃቸው አንችልም። መጽሐፍ ቅዱስ በጴጥሮስ መልእክት በኩል ግን << የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ በዙሪያችሁ ይዞራል >> በማለት ከባቢያችን ላይ የሚያንዣብቡ ጠላቶች እንዳሉ ቁልጭ ባለ ቃል አስቀምጦልናል። ከሩቅ ያያችኋል አይደለም የሚለው። በዙሪያችሁ ይዞራል ነው የሚለው። በእያንዳንዱ የዕለት ተዕለት የኑሮ አጋጣሚዎቻችንና ጉዞዋችን ውስጥ ብዙ የምንዞርባቸው ዙሪያዎች አሉን። እንደው ስለለመድነው አናስተውል ይሆን እንጂ በእያንዳንዱ ቦታ በሆነ ሰዓት ላይ የመገኘታችን ፋይዳ በኋላ በሕይወታችን ውስጥ የራሱን ትርጉምና ፍቺ ይዞ ሲገኝ ቆይቶ የምንረዳው ይሆናል። በዚህ በመውጣት በመግባታችን መካከል ታዲያ የምድርን ኗሪነት የምንሳተፈው እኛ ብቻ አይደለንም። ወደ ምድር የተጣሉትም ርኩሳን መናፍስትም አብረውን የሚኖሩ ፍጡራን ናቸው። ለዚህ ነው << ባላጋራችሁ ዲያቢሎስ >> ሐዋሪያው ያለው። ባለ-ጋራ ነው የሚለው። የሚጋራ ማለት ነው። ከሚጋራቸው ነገሮች ውስጥ አንደኛው ክፍል ምድርን ነው። አልፎም ተርፎ በምድር ላይ የሚኖሩትን የሰው ልጆች ትውልድ ዘመንን፣ ግዜን፣ ኑሮን፣ አሳብን፣ ሕሊናን፣ ልቦናን፣ ሰውነትን፣ ዕድልን፣ ጸጋን፣ እውቀትን፣ ገንዘብን፣ በረከትን፣ ሞገስን፣ ቤትን፣ ቤተሰብን ሁሉ የሚጋራ ነው። ተጋርቶህ ሲኖር ሊያሻሽልህ ወይ በደረጃ ከፍ ሊያደርግህ አይደለም የሚቀመጠው። የተጋራህን ነገር ሁሉ ሊያጠፋውና በመጨረሻውም አንተን ሊያጠፋ ነው የሚታገለው።

✞✞✞

በመሆኑም ክርስቲያን የፈለገ ይምጣ ቢያንስ ጠዋት ከቤት ሲወጣና ማታ ወደ ቤት ሲመለስ መጸለይ፣ መስገድና በመቁጠሪያ መፈተሽ ያለበት ለዚህ ነው። ጠዋት ከቤት ሳይወጣ ጸልዮና ሰግዶ፣ መዝሙር 90(91)'ን አንብቦ፣ ቅባዕ ቅዱስ ተቀብቶ ወደ ሥራው አሊያ ወደ ትምህርቱ መሄድ ይኖርበታል። እንደዚህ በሚያደርግበት ግዜ መንገድ ላይ የሚያንዣቡ መናፍስት፣ በየሰው ዓይን ውስጥ ቡዳ የሆኑ መናፍስት፣ አስፓልትና ቱቦ ዙሪያ ሱሉስ(የዝውውር ቁራኛ) የተደረጉ መናፍስት እና ወዘተ... አይቀርቡም። ጠዋት የጸለየው መዝሙር 90(91) ይከተለዋል። << በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አስር ሺህ ይወድቃሉ። ወዳንተ ግን አይቀርቡም! >> የሚለው ቃል በጠባቂ መልአክቶች በኩል እየጸደቀ ይከተለዋል። << ክፉ ነገር አይቀርብም፤ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም >> የሚሉት ቃላት ጠዋት በሰገደው የአምልኮት ስግደት በኩል ስለሚታዘዙ ሰውየው እርሱ ከማያያቸው ከክፉ ነገራት ሁሉ እየተጠበቀ ቀኑን ይውላል። ማታ ደግሞ ወደ ቤት ሲመለስ ወደ እንጀራው መሮጥ አይደለም። ወደ አልጋው መርጥ አይደለም። ቀኑን በሰላም ያሳለፈን ጌታ በሰላም እንዲያሳድረን ደግሞ እንበረከካለን። አሁን ማታ ደግሞ የፍተሻ ግዜ ነው። በቀን ውሎው ውስጥ ሰውየው

የማይነካው እቃ አይኖርም። በተለይ በንግዱ ሥራ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎች በጣም መጠንቀቅ ያስፈልጋቸዋል። ከተለያየ ሰው የሚቀበሉት ገንዘብ ከማን እንደመጣ የሚያውቁት ነገር የለም። ከጠንቋይና ከድግምተኞች የተገኘ ገንዘብ ይሆናል። ከመተተኞችኛ ሟርተኞች የተወሰደ ገንዘብ ይሆናል። የድሆቸን ደም አሊያ እምባ በማፍሰስ የመጣ ገንዘብ ሊሆን ይችላል። ገንዘቡ ውስጥ እንደተከናወነበት የግፍ ሥራና የባዕድ አምልኮት ግብር፤ ያንኑ ክፉ ጠባዩን ለተቀባዩ አውርሶ ከፊት እየቀደመ እርም የሆነ ግዜን፣ ጭንቅ የሆነ ኑሮን፣ አልፈታ ያለ ውቻንብር የሚያስከተል የሕይወት አጋጣሚዎቸን ሊፈጥር ይችላል። ዛሬ ገንዘብ ተቀብለን ካዝና ውስጥ ለመቆለፍ እንጂ በእግዚአብሔር ኃይል ለማስባረክ አንቸኩልም። ስለዚህ ገንዘቡም በራሱ የግፈኞችና የአመፀኞች ንብረት ስለሆነ አይበረክትም። ዘንድሮ ከትላልቅ ደሞዝተኞች እስከ ቀን ገቢ የሚያገኙ ሰዎች እኩል ያማርራሉ። እንዴ ጥሩ የሚሠራውም የማይሠራውም ኑሮ እንዴት እኩል ይከብደዋል ብለን ስናስብ፤ በረከት ያጣ ግዜና ኑሮ የሚፈጥሩት በረከት አልባ ገንዘብና ሐብት በመሆኑ ነው። በእግዚአብሔር በኩል አልባረክ ያለ ኑሮ ውስጥ ረድኤትና እርካታ ይኖራል መጠበቅ በምንም መልኩ አይቻልም።
ስለዚህ ማታ ወደ ቤት ስንገባ በጸሎት በታቸን እንፈትሻለን። "በቀን ውሎዬ ውስጥ የገባህ፣ በነካሁት ነገር ተወራርሰህ የተቆራኘህ፣ ከሰው ዓይን የመጣህ፤ በጌታቸን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተይዝሃል፤ በድንግል ማርያም ስም ተይዝሃል። በሥላሴ ስም ከየት እንደመጣህ ተናገር" እያልን ጀርባንና ሆድን ሌሎቸም የሰውነት ክፍሎች ላይ ስንቀውረው ገና የገባ መንፈስ ስለሆነ ወዲያው የመጋለጥ ዕድሉ ከፍተኛ ነው። ከዛ በቅባ ቅዱስ ግንባር ላይ አስረነው "ትወጣለህ አትወጣም?" እያልን እየሰገድን እና በመቁጠሪያ እየነረትን ስንበጠብጠው ሐይወታችንን መልመድ ስለሚያቅተው ቶሎ ይወጣል።

✞✞✞

ሌላው በአከባቢ ውስጥ ስለሚደበቁ መናፍስት ስንመለከት፤ ከየሰዉ ዓይን የሚነሣው መንፈስ ሕይወታችንን በስውር አጥቅቶ ከንቱ እንዳደረገን በተገባ አልተገነዘብንም። ብዙ በተለይ ሴት እህቶቻችን ይሸወዳሉ። የተበጣጠቀ ሱሪና የተቀረጠፈ ቀሚስ ለብሰው፣ ያገኙትን መዋቢያ እቃዎች ሁሉ ተጠቅመው ሲወጡ የሚያያቸው ሰው ብቻ ይመስላቸዋል። ግን ሥልኩ ላይ በቀረጸው የወሲብ ፊልም ምስል በኩል እያነጻጸረ የሚያያቸው ወንድ ላይ ሆኖ አብሮ ከንፈር የሚያረጥበው ቡዳ የሚሆነው መንፈሱም ጭምር ነው። አንዳንድ ግዜ ሰዎች ቀን ከማያውቁት መንገደኛ ጋር ማታ አብረው በሕልማቸው ሊያድሩ ይችላሉ። እኔም ተሞክሮአቸውን ያካፈሉኝ የማውቃቸው ሰዎች አሉ ቀን ካዩት የማያውቁት መንገደኛ ጋር ማታ የሚተኙ። እንደዚህ ሲሆን ሁለት ምክንያት አለ ማለት ነው። አንደኛው የመንገደኛው መንፈስ ቡዳ ሆኖ በልቷቸዋል። ሁለተኛው ከውስጥ ያለው መንፈስ ያየነውን ሰው ቀርጾና ምስል አሲዞ አምጥቶትም ይሆናል። በገሃድም ከብዙ ሴቶችና ወንዶች ጋር በቀላሉ የሚተኙ ሰዎች የራሳቸው ተቃራኒ ጾታን የመሳብ ችሎታ፣ ዕድልና ገድ ይመስላቸዋል። ምናልባት ጓደኞቻቸውም እንደ ትልቅ ጀብዱ እየቆጠሩላቸው "እርሱ እኮ ያያትን በአንዴ ነው የሚያወጣው!" እያሉ መናፍስታዊ ድበቃው ላይ አስተዋጽኦ ያዋጣሉ። አንድ ግዜ ባለትዳሮች ባሉበት ክፍል ውስጥ የተገኘች አንዲት ልጅ፤ ከባለትዳሩ ሰውየ ጋር በተያየች ቁጥር ሰውየውን ሳታውቀው ወደርሱ በጣም ትሳባለች። በኋላ እንደ አጋጣሚ ሆኖ የባልየው መንፈስ ሲያዝ ውስጡ የነበረው ቡዳ ምን አለ << ሰውየው የሚያያትን ልጅ ቡዳ ሆኜ ልበላት ነበረ! ከዛ በቀላሉ እጁ ትገባለች አለ >>። ይኸው እንግዲህ መናፍስት የዚህን ያህል የዕለት ተዕለት የሰዎች ኑሮ ውስጥ ዘልቆ ይገባሉ። ይሄ ባለትዳር ለረጅም ግዜ የሴቶች ግምባር ያለውና የሚፈልጋትን ሴት በማየት ብቻ መኃተት መቻሉ እንደ ዕድለኛና የተለየ ተመራጭ አድርጎ ራሱን እንዲቆጥር አድርጎት ነበረ። እሺ ዛሬ በእንደዚህ አይነት መንፈስ ስንቶች ተጠቅተዋል?

✞✞✞

 አከባቢ ላይ ከሚያደፍጡ መናፍስት ሌላኛው ክፍል የመቃብሩ መንፈስ(ከልከልዮስ) ይጠቀሳል። የሞት አበጋዝ የሆነ የጨለማ መንፈስ ስለሆነ ከመቃብር አይጠፋም። አባቶታችን በቀደመው ዘመን ስለነዚህ መናፍስት ሃይማኖታዊ ግንዛቤ ነበራቸው። "ከመሸ ወደ መቃብር አትሂዱ! ትለከፋላችሁ።" በማለት ያስጠነቅቁ ነበረ። መለከፍ ማለት መቃብሩ ዙሪያ የሚያንዣበው ጠላት ከሰውየው ጋራ ቁራኛ ለመሆን ወደ ሕይወት የሚመጣበት መንገድ ማለት ነው። አንዳንድ ግዜ ሰዎች ከቀብር ሥነ ስርዓት በኋላ ራሳቸውን ይታመማሉ። ከዛ በኋላ የጤና መቃወስ፣ ጭንቀትና መፍዘዝ ምልክቶችን ሊያሳዩ ይችላሉ። ይሄ አንደኛው የሚያንዣብቡ የአከባቢ መናፍስት ወደ ዘመናቸው ስለመምጣታቸው የሚነግር ምልክት ሊሆን ይችላል። ጨለማ የበላን ትውልዶች ነን እያችሁ።

✞✞✞

 ይኸውላችሁ በወንጌለ ዮሐንስ ምዕ 8፥12 ላይ እንደዚህ የሚል የተስፋና የኃይል ቃል እናገኛለን። << እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም >>

በቃ በምን አይመላለስም? በጨለማ አይመላለስም። ዛሬ ዓለማችን በብዙ መንገድ በጨላማው መንገድ ውስጥ ርቀትን ተጉዛ፤ ምድሪቱ በጽልመት ተውጣ፤ ወዴት እንደሚሄድ ፍንጭ ያጣ፣ የት ቢሄድ ብርሃን እንደሚያገኝ መረጃ የሌለው፤ ይቁም ይሂድ እንኳ መለየት ያቃተው የሰው ልጆች ትውልድ እየበዛ መጣ። ጉዞ የሌለው ትውልድ፣ ጉዞ የሌለው አገር፣ ጉዞ የሌለው ዜጋ በቃ። በጨለማ ብቻ የሚሄድ ዓለም።

 በኛም አገር ታዲያ ኢትዮጵያውን ከአባቶቻችን የብርሃን መንገድ ተነጥለን ያዋጣናል ባልነው መስመር አቆራርጠን መጥተን፤ በኋላ መቼ እንደወረሰን ያላወቅነው የዲያቢሎስ ሠራዊትና የእርግማን ጨለማ ቢወረን ጊዜ፣ መሄጃ አጣን። ጨለማ ውስጥ ያለ ሰው ወዴት እንደሚሄድ ለማወቅ እንዲችል ብርሃን ያስፈልገዋል። ይህንን ብርሃንን ያጣነው እኛ ታዲያ ውስጣችንም ውጪያችንም ማየት ስላቃተው አጠገባችን ካለው ሁሉ ጋር በእውር ድንብር እየተጋጨን፣ እርስ በእርስ እየተነካከስን፤ የአንዱን መንገድ አንዱ እያፈረሰ፣ የአንዱን ጉዞ ሌላው እየተጓዘ፣ የአንዱን ዕድል ሌላው እየቀማ፤ ከጨለማ ወደ ባሰ ጨለማ፤ ከመደነጋገር ወደ መተረማመስ፤ ከመሰብሰብ ወደ መበታተን እየተሸጋገርን መጣንና አሁን ብርሃናችን በጥቂቶች ህልውና ውስጥ ተሸጉራ፤ የተቀረነው ግን ጨለማ ውስጥ ተቀምጠን አበሳችንን ከቀን ቀን እንቆጥራለን። እግዚአብሔር ይማረን።

 ✝ ወስብሐት ለእግዚአብሔር
 ✝ ወለወላዲቱ ድንግል
 ✝ ወለመስቀሉ ክቡር

✝ እንግዲህ ብልጥ ሁኑ። እንደጋዜጣ አንብባችሁ ቁጭ አትበሉ። መንፈስ የሚደበቅበትን ቦታዎች ሁሉ ማፍረስ ላይ ከበረታችሁ፤ የሚደበቅበትን ስለሚያጣ በቀላሉ የመገለጥ አጋጣሚው ይሰፋል። ታሸንፉትማላችሁ። አንብባችሁ መቀመጥ ከሆነ ያው በቃ ቁጭ ያላችሁበት አኗኗር በሕይወት ውስጥ ተተርጉሞ ቁጭ ያለ በረከት፣ ቁጭ ያለ ጸጋ፣ ቁጭ ያለ ሰላምና ግዜ ባለቤት ትሆናላችሁ።
ስለዚህ አስተውሉ!

በሚቀጥሉት
☞ <u>ስለ ቅዱስ ቁርባን በሰፊ ክፍሎች</u>

☞ <u>ክፉ መንፈስን ስለሚረበሹ ባህሪያትና ልማዶች</u>

☞ <u>ጸሎት መጽሐፍን እንዴት ከዲያቢሎስ ውጊያ አንፃር ነቅተን እናብብ</u>

የሚሉ ርእሶችን ከቃለ ወንጌሎች ጋር እንደፈቃዱ እግዚአብሔር ይኖሩናል! በርቱ!

መናፍስት ላይ ንቁ
#ጸባኦት_ይከተላችሁ
@abat_memhir_girma